DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

*As of Jan 31, 2018*

# ኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከወላጆች እና ከቤተሰቦች ተዘውትረው የሚነሡ ጥያቄዎች

**(Coolidge High School Frequently Asked Questions from Parents and Families)**

## አጠቃላይ ገጽታ

በአሁኑ ወቅት ኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Coolidge HS) በግንባታ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በነሀሴ (August) 2019 ይጠናቀ ቃል ተብሎ የሚጠበቅ የግንባታና ዘመናዊ የማድረግ ሥራ እየተካሄደ ነው። በዚህ ጥገና ወቅት፣ ዲሲፒኤስ ታታሪነትን በሚያጎለብት፣ ከማኅበረሰብ ፍላጎት ጋር በማቀናጀት እና በማጣጣም የተማሪዎችን ምዝገባ እጅግ ከፍ በሚያድረግ ዐላማዎች ላይ በመንተራስ፣ በትምህርት ቤት ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርቶች የሚሰጥባቸውን መንገዶች ለመቀየስ እና ለማጠናከር ጊዜ እየወሰደ ነው። አዲስ መካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመከፈት በተጨማሪ፣ ሁለተኛ ደረጃው ትምህርት ቤት የጤና ሣይንስ አካዳሚ፣ የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች አካዳሚ፣ እና የመጀመሪያ ደረጃ የኮሌጅ አካዳሚዎችን በማካተት በ 2019 እንዲከፈት ይደረጋል።

## በኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Coolidge High School) የአካዳሚዎች ገጽታ

| የአካዳሚው ስም | ማብራሪያ | የምዝገባ መስፈርቶች |
|---|---|---|
| የጤና ሣይንሶች አካዳሚ | • **ኮርሶች፤** የሣይንስ ኮርሶች እና የኮሌጅ ዝግጅት ትምህርቶች<br>• **የኮሌጅ ተጓዳኞች፤** ፋኩልቲ/የመምህራን ተጓዳኞች፣ የመንታ ምዝገባ ትምህርቶች<br>• **የሙያ ተጓዳኝነቶች፤** የኢንዱስትሪ ቦርድ የሚደግፉቸው ንግግር አድራጊ እንግዶች፣ ቦታውን ጎብኝዎች፣ ገንዘብ የሚከፈላቸው ተጓዳኞች<br>• **የብቃት ምስክርነት ማረጋገጫዎች፤** የተመሰከረላቸው የነርስ ረዳቶች የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪዎች | የክልል እና መጋቢ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የመማር እድሎች ይኖሯቸዋል |
| የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች አካዳሚ | • **ኮርሶች፤** የጋዜጠኝነት ሙያ እና የጽሑፍ ትምህርት አማራጭ ትምህርቶች + የኮሌጅ ዝግጅት ኮርሶች<br>• **የዩንቨርሲቲ ቅንጅት፤** የመንታ ትምህርት ምዝገባ ኮርሶች<br>• **የሙያ ቅንጅት፣** የኢንዱስትሪ ቦርድ ተጋባዥ እንግዶችን ይደግፋል፣ የቦታ ግብኝቶችን፣ እና ተጓዳኝነት ቅንጅቶች።<br>• **ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፤** አዶቤ ፕሪሚየር ፕሮ እና አፍተር ኢፌክትስ (Adobe Premier Pro & After Effects) | የክልል እና መጋቢ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የመማር እድሎች ይኖሯቸዋል |
| የመጀመሪያ ደረጃ የኮሌጅ አካዳሚ | • **ኮርሶች፤** የ 9 እና 10 ክፍል በሁለተኛ ደረጃ ያሉ ሲሆን፣ የላቀ ምደባ የቅድሚያ ምደባ እድል የሚሰጥ። የ11ደኛ እና 12ተኛ ክፍል ተማሪዎች ከዩንቨርሲቲ ተጓዳኞች ጋር የኮሌጅ ኮርሶችን እስከ 60 ክሬዲት 12ተኛ ክፍል ማብቂያ ድረስ መውሰድ ይችላሉ። | በትምህርት ቤቱ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት ከተማ አቀፍ የማመልከት ፕሮግራም |

**በኩሌጅ ምን ዐይነት ዘመናዊ የማድረግ ተብራ እየተከናወነ ነው?**

አሁን ያለው ሕንጻ የትምህርት ክፍሎችን ስፋት በትክክል ለመመጠን እና ዘመናዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ሙሉ የውስጥ ግድግዳዎችን የማፍረስ እደሳ ይደርግለታል። ከሕንጻው በስተጀርባ ያለው የመጫዎቻ ስፍራ ዙሪያውን እንዲዘጋ ተደርጎ ከላይ ብርሀን የሚያስገባ ባለመስተዋት ጣሪያ ተደርጎ ይታደሳል። ከሕንጻው በስተጀርባ ያለው የመጫዎቻ ስፍራ ዙሪያውን ይዘጋ እና ለአዲሱ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ለመዋዕለ ሕጻናት የሚሆን አነሥተኛ ተጨማሪ ጣራ ያለው መግቢያ መተላለፊያ በስተደቡብ በኩል ባለው ቦታ ላይ እንዲገነባ ይደረጋል።





**የኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የኩሌጅ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስተዳደር አመራር መዋቅር ምን ይመስላል?**

- **ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤** አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሠ መምህር፣ ሁሉን አካታች እና ከሌሎች ጋር የተቀናጀ፣ የተጣጣመ የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ በሦስት አካዳሚዎች (በመጀመሪያ ደረጃ ኮሌጅ፣ የጤና ሣይንሶች፣ እና የብዙኃን የመገናኛ ዘዴዎች አግልግሎትን) በበላይነት የሚቆጣጠር ይሆናል።
- **የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤** የመለስተኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስኬታማነት ባለው መልክ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሸጋገራቸውን እውን ለማድረግ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሠ መምህር ጋር በቅንጅት የሚሠራ የራሱ ርእሠ መምህር ይኖረዋል።

**የኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሌሎች የአካዳሚክ ትምህርት ተማሪዎች መቼ ነው በትብብር የሚቀናጁት?**

ተማሪዎች ሁሉ፣ ሥነ ጥበብ፣ ሙዚቃ፣ የሰውነት ማጎልመሻ እና ሌሎች በምርጫ የሚወሰዱ (electives) ትምህርቶችን አንድ ላይ ከሌሎች ጋር አብረው ይወስዳሉ። በተጨማሪም ተማሪዎች ሁሉ፣ ከትምህርት በፊት እና ከትምህርት በኋላ በሚካሄዱ ክበቦች ተሳትፎን ጨምሮ፣ በስፖርቶች እና በተጨማሪ የትምህርት ዐይነቶች (extracurriculars) ትምህርት እንዲሳተፉ ይደረጋል።

**የመለስተኛው ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለእነዚህ ለኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአካዳሚክስ ትምህርቶች ተዘጋጅተው የሚመጡት እንዴት ነው?**

- የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተሰናድተው እና ዝግጁ ሆነው በኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተዋጣላቸው እንዲሆኑ፣ የኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ርእሠ መምህሩና የአካዳሚክ ትምህርት ሥራ አስኪያጆችን የሚያካትተው የትምህርት ቤቱ የአመራር ቡድን የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስኬታማ ለመሆን የተዘጋጁ መሆናቸውን  እውን ለማድረግ ቡድኑ ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሠ መምህር እና ከእሱ/እሷ የአመራር ቡድን ጋር በቅርብ ሆኖ በመተባበር አብሮ አንድ ላይ ይሠራል ወይንም ትሠራለች።
- በመለስተኛ እና በሁለተኛ ደረጃው ትምህርት ቤቶች መካከል ለተማሪዎች ትብብር እና አንዱ የሌላው ጠባቂ አስተማሪ በመሆን ለሚያደርጉት ድጋፍ እና እንዲሁም የመምህራን የትብብር እድሎች ይኖሯቸዋል።

**መምህራን እና ማኅበረሰቡ በዚህ ሂደት እንዴት ነበር በሥራ ላይ ተሰልፈው የነበሩት?**

ዲሲፒኤስ በተማሪዎች የትኩረት ቡድኖች፣ በወላጆች እና በመምህራን፣ በኩሌጅ የሥራ ቡድን፣ የማኅበረሰብ ስብሰባዎች እና በኦን ላይን ላይ የአሰሳ መጠይቆች አማካይነት በሙቶ የሚቆጠሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሁሉ በተግባር ላይ አሰልፏል። በተጨማሪ፣ በቅርቡ በቀጠና 4 የትምህርት የትብብር ቅንጅት የኅዳር ስብሰባ (Ward 4 Ed Alliance November meeting) አካሂዷል።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

**የእንጊሊዘኛ  ቋንቋ ተማሪዎች፣ በሦስቱ አካዳሚዎች በአንዱ ለማመልከት እና ትምህርት ለመማር ይችላሉ ወይ? ከሆነስ እንዴት ነው የእንጊሊዘኛ ትምህርት ድጋፍ ሊኖር የሚችለው?**

የእንጊሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች (ELs) ለአካዳሚክ ኮርሶች ለማመልከት እና ለመሳተፍ ይችላሉ። የእንጊሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሙሉ፣ በእንጊሊዘኛ ቋንቋ የቅልጥፍና ብቃት መጎናጸፍን አመልካች በሆነው በ ACCESS 2.0 ግምጋማ ደረጃ 5.0 ላይ እስከሚደርሱ ድረስ፣ የእንጊሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ (ESL) አገልግሎቶች የማግኘት እድል አላቸው። የእንጊሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የትምህርት አሰጣጥ አገልግሎቶች፣ ተወዳዳሪ የሌላቸው የቋንቋ ማዳበሪያ ትምህርቶች፣ የይዘት ቋንቋ ማዳበሪያ ትምህርቶች፣ የይዘት ቋንቋ እና የራስ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥጥ አካል የሚቀናጁበት የቋንቋ እና የይዘት/በምርጫ የሚወሰዱ ትምህርቶችን ቅርጽ ሊይዙ ይችላሉ። ተገቢ የድጋፍ ትብብር አግልግሎቶች ጥረት በቦታው የሚገኙ ለመሆናቸው እርግጠኛ ለመሆን፣ በኩሌጅ ትምህርት አመራር እና የቋንቋ ትምህርት ዋና ክፍል (Language Acquisition Division) አማካይነት፣ የእንጊሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎቶች የሚገኙ ከሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቅርጽን ሊወስዱ የሚችሉ ሲሆን የኮርሶች ምደባ እና የትምህርት አሰጣጥ ክፍለ ጊዜያት ድልደላ እንዲካሄድ ይደረ ጋል። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ Rosanna.demammos@dc.gov አማካይነት ግኑኝነት ያድርጉ።

**ለምንድን ነው ዲሲፒኤስ የመጀመሪያ ደረጃ የኮሌጅ ትምህርት ፕሮግራም በኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ላይ የሚያከልው?**

የዲሲፒኤስ ራዕይ የመጀመሪያ የኮሌጅ ትምህርቶችን በከተማይቱ በመላ ከዳር እዳር እጅግ በጎላ ደረጃ ለማዳረስ ነው። በአሁኑ ጊዜ የመጀመሪያ የኮሌጅ ትምህርት የሚሰጠው በስኩል ዊዛውት ዎልስ (School Without Walls) ነው። የኩሌጅ ማኅበረሰብ በጣም የጎለበቱ የትምህርት አሰጣጦችን፣ ለኩሌጅ ትምህርት ዝንባሌ ያለው መሆኑን የገለጸ ሲሆን ከዚህም በላይ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ለኩሌጅ ክልል ትምህርት ቤታቸው የሆኑ ከቀጠና (Ward) 4 ውጪ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተማሩ ነው። ለተለያዩ የከተማይቱ ክፍሎች የዚህ ፕሮግራም መዳበር ግብአት ኩሌጅ ታላቅ እጩ እንደሆነ እናምናለን።

**ወላጅ፣ በሎተሪ እጣው አማካይነት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ኮሌጅ አካዳሚ ለመግባት ማመልከት ያለባቸው መቼ ነው?**

ወላጆች ለመጀመሪያ ኮሌጅ አካዳሚው በትምህርት ቤቱ ዲሲ የሎተሪ እጣ (My School DC Lottery) አማካይነት ያለመክታሉ። ትምህርት ቤቱ ለትምህርት ዓመት 19-20 የመጀመሪያ 9ኛ ክፍሉን የሚመዘግብ ሲሆን፣ ይህም ማለት የአሁኑ ወቅት (የትምህርት ዓመት (17-18) 7ተኛ ክፍል ተማሪዎች ወደ መጀመሪያው ኮሌጅ አካዳሚ ለመግባት ቀዳሚዎች ይሆናሉ። ፍላጎት ያላቸው ወላጆች፣ በመጸው (Fall) 2019 ከሚከፈተው አካዳሚክ በፊት፣ በየካቲት (February) 1, 2019 በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ ዕጣ አማካ ይነት ቀደም ብለው ማመልከቻዎቻቸውን እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ።

**አንድ ተማሪ ከአንዱ አካዳሚ ወደሌላው አካዳሚ ለመዛወር ይችላል ወይ? ይህ የሚፈቀደው መቼ ነው?  በእጋማሽ ዓመት ላይ ወይንስ በአዲስ ክፍል መጀመሪያ ላይ?**

በመጭው ዓመት በአካዳሚዎች መካካል የዝውውር ፖሊሲዎችን የምንወስን ሲሆን፣ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመወሰን የእናንተን ሀሳብ እና አስተያየቶች ለመስማት እጅግ ደስተኞች ነን።

**የበለጠ ጥያቄዎች አሉዎት?**

ይህ በቤተሰብ ላይ እንዴት ጫና እንደሚያሳድር የበለጠ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይንም የበለጠ ዝርዝር ጉዳዮችን የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክ ዎን የትምህርት ቤት የእቅድ ቡድኑን በ DCPS.Planning@dc.gov. ለማግኘት ይሞክሩ።

- በተጨማሪም ብሎጋችንን (blog) በ https://dcpsplanning.wordpress.com/category/coolidge/ መቃኘት ይችላሉ።
- ከዚህም ሌላ በትዊተር (twitter) @DCPSPlanining አማካይነት ሊከታተሉን ይችላሉ።